አይንዋን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በጨለማ ፡ አፍጣ ። በዚያ ፡ አይን ፡ ቢወጉ ፡ በማይታይበት ፡ ጨለማ ፡ በዛብህን ፡ ብቻ ፡ ታይ ፡ ነበር ። በዛብህ ፡ ብቻ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀጭ ፡ ብሎ ፡ ሲያወራ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አይኖቹን ፡ ጭፍን ፡ ጉንጮቹን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ሰርጎድ ፡ አድርጎ ፡ ሲስቅ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እጅዋን ፡ ተጠንቅቆ ፡ ይዞ ፡ ሲያስጽፋት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አይኖቻቸው ፡ በጎን ፡ ሰርቀው ፡ ሊያዩ ፡ ሲሞክሩ ፡ ድንገት ፡ ይጋጩና ፡ የሱ ፡ ቀድመው ፡ ሲሸሹ ፡ ወዲያው ፡ የሱ ፡ አደነጋገጥ ፡ ጭምር ፡ እዬተለዋወጠ ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ይታያት ፡ ነበር ።

"በመሄዱ ፡ ቆርጦ ፡ ይሆን ? አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢመጣ ፡ ባይሆን ፡ ቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ ትምርቴን ፡ እስክጨርስ ፡ እንዲቆይ ፡ እነግረው ፡ ነበር ! ብቻ ፡ እንዴት ፡ ብዬ ፡ እነግረዋለሁ ? እባክህ - - -- - -ትምርቴን ፡ እስክጨርስ ፡ እንኩዋ ፡ - - - - -ቆይልኝ ! የለም ፡ እንኩዋ - - - -ስል ፡ አብሪያት ፡ እንድኖር ፡ ፈልጋለች ፡ ይላል ! እባክህ ፡ ትምርቴን ፡ አስጨርሰኝና ፡ ሂድ ፡- - - ! ይህ ፡ ይሻላል !" አለች ፡ ሰብለ ፡ ምናልባት ፡ በዛብህ ፡ የመጣ ፡ እንደሆነ ፡ ራስዋን ፡ ሳታጋልጥ ፡ አብሮዋት ፡ እንዲቆይ ፡ የምትጠይቅበትን ፡ ቃል ፡ መምረጥ ፡ አቅቶዋት ፡ ስትቸገር ፡ ቆይታ።

ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ የበዛብህን ፡ ነገር ፡ ስታነሳ ፡ ስትጥል ፡ እንቅልፍ ፡ ሳይወስዳት ፡ እስከነኩለ ፡ ሌሊት ፡ ቆይታ ፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ቅገርት ፡ የሞላበት ፡ የማያሳርፍ ፡ እንቅልፍ ፡ ተኛች ። በዛብህ ፡ በበነጋውም ፡ ለምሳ ፡ አልመጣም ። ብቻ ፡ አባ ፡ሞገሴ ፡ ጥዋት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ክርስቲያን ፡ ሲሄዱ ፡ በቤቱ ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ በተቀዳሚው ፡ ቀን ፡ ሳይመጣ ፡ በመቅረቱ ፡ ጌቶችም ፡ እሜቴም ፡ መስጋታቸውን ፡ ነግረውት ፡ ወዳጁ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ ታመመ ፡ ለመጠዬቅ ፡ ሄዶ ፡ የነበረ ፡ መሆኑንና ፡ ክሰአት ፡ በሁዋላ ፡ ለማስተማር ፡ የሚመጣ ፡ መሆኑን ፡ እምሳ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተናገሩ ፡ የሁሉም ፡ አሳብ ፡ ትንሽ ፡ አረፍ ፡ አለ ።

# ምእራፍ ፡ ፲፰ ፡
# የባላገር ፡ መላክተኞች ፡

በዛብህ ፡ ከምሳ ፡ በሁዋላ ፡ ለማስተማር ፡ የሚመጣ ፡ መሆኑን ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ እማብር ፡ ላይ ፡ ሲናገሩ ፡ ቤተሰቡን ፡ በሙሉ ፡ ደስ ፡ አለው ። ፊታውራሪ ፡ እንኩዋ ፡ ምንም ፡ ሰብለን ፡ አንቺ ፡ ማለቱ ፡ ትልቅ ፡ ስተት ፡ መሆኑን ፡ ቢያውቁ ፡ ወደዚህ ፡ ስተት ፡ የመሩት ፡ ምሽታቸውና ፡ ልጃቸው ፡ በመሆናቸው ፡ ለሱ ፡ ይቅርታ ፡ ያደረጉለት ፡ መሆናቸውን ፡ ሲመጣ ፡ አስጠርተው ፡ ሊነግሩ ፡ አስበው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እነማይ ፡ ውስጥ ፡ ካሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጉልቶቻቸው ፡ ጥቂት ፡ ባላገሮች ፡ ድንገት ፡ ስለመጡ ፡ እነሱን ፡ ሲያዩ ፡ በዛብህን ፡ ረሱት ።

ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሊሆን ፡ ትንሽ ፡ ሲቀረው ፡ አጋፋሪው ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ከሶስት ፡ ጉልቶቻቸው ፡ ሶስት ፡ የባላገሮች ፡ ወኪሎችና ፡ ሹማቸው ፡ ብላታ ፡ መንግስቱ ፡ ዘላለም ፡ መምጣታቸውን ፡ ሲነግራቸው ፡-

"እሀ ! መጡ ? ምሳቸውን ፡ አብላቸው ።" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡

"እዳራሽ ፡ ይብሉ ፡ ወይስ ፡ እዚህ ?" አለ ፡ አጋፋሪው ፡ ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሊሆን ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ ያልቀረው ፡ መሆኑን ፡ በመመልከት ።

"እእ - - - -ግዴለም ፡ እዚህ ፡ አብላቸው !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ።

መጀመሪያ ፡ ሹሙ ፡ ከዚያ ፡ የባላገሮች ፡ ወኪሎች ፡ ተጠርተው ፡ ገብተው ፡ ምሳቸውን ፡ በልተውና ፡ አንዳንድ ፡ ብርሌ ፡ ጠላ ፡ ጠጥተው ፡ እስኪወጡ ፡ ድረስ ፡ ፊታውራሪ ፡ በቁጣ ፡ በቀላ ፡ ክፉ ፡ አይን ፡ ይመለከቱዋቸው ፡ ነበር ።

ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሆኖ ፡ አዳራሽ ፡ እንደ ፡ ተነጠፈ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቶሎ ፡ እዚያ ፡ ሄደው ፡ ተቀምጠው ፡ ባላገሮች ፡ እንዲጠሩ ፡ አዘዙ ። ቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ባላምባራስ ፡ ምትኩ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ እዛኝ ፡ ደስታ ፡ ሌሎችም ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆቻቸው ፡ ነበሩ ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሰብለ ፡ በምትማርበት ፡ ሄዶ ፡ አክስቱንና ፡ እስዋን ፡

እረፍት ፡ ሳያምረኝ ፡ ወገቤን ፡ ሳልፈታ ፡
አንተን ፡ ተከትዬ ፡ ከጥዋት ፡ እስከ ፡ ማታ ፦
በጎንቻ ፡ በርሀ ፡ ልበል ፡ ገልታ ፡ ገልታ ፦
እንቅፋት ፡ ሲመታህ ፡ አብሬህ ፡ ልመታ ፦
አበጀ ፡ በላቸው ፡ የመብቱ ፡ ጠባቂ ፡ ያርነቱ ፡ ጌታ ፦
“ ምጣዴን ፡ አዝዬ ፡ እርኮቴን ፡ እንግቼ ፦
ሽንብራ ፡ ቆርጥሜ ፡ ጥሩ ፡ ውሀ ፡ ጠጥቼ ፦
ራበኝ ፡ ደከመኝ ፡ ሳልል ፡ ተገዝቼ ፦
ባለጸጋ ፡ ባሌን ፡ ዛሬውን ፡ ፈትቼ ፦
እሱን ፡ እንደከተል ፡ ቤት ፡ ንብረቱን ፡ ትቼ ፦
የግሩ ፡ እጣቢ ፡ እንድሆን ፡ ግርድና ፡ ገብቼ ፦
አበጀን ፡ አማልዱኝ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆቼ ፦
“ የራስ ፡ የደጃዝማች ፡ ምሽት ፡ ከመሆኔ ፦
አሽከር ፡ ከመላኬ ፡ ሲጋር ፡ ከማስጫኔ ፦
ስባንን ፡ እንድኖር ፡ ሳይከደን ፡ አይኔ ፦
እንቅልፍ ፡ እንዳልጠግብ ፡ ተኝቼ ፡ በጎኔ ፦
የሱ ፡ ገረድ ፡ ሆኜ ፡ ልኖር ፡ መለመኔ ፦
ወንድ ፡ ብወድ ፡ ነው ፡ ሴት ፡ ስለሆንሁ ፡ እኔ ፦
“ ስማኝ ፡ ያገሬ ፡ ወንድ ፡ ልውቀስህ ፡ ወቀሳ ፦
አይደለህ ፡ ቀማኛ ፡ አይደለህ ፡ ጀውሳ ፦
ሳትሰርቅ ፡ ሳትቀማ ፡ ሳይኖርህ ፡ እበሳ ፦
እየነዱ ፡ ሲያስሩህ ፡ እንዲሁ ፡ ባፈሳ ፦
የማትፈራገጥ ፡ የማትንቀሳሳ ፦
ትንሽ ፡ የማትሻክር ፡ ከሆንህ ፡ ለስላሳ ፦
በሁለት ፡ እግሩ ፡ ቆሞ ፡ ከሚሄድ ፡ እንስሳ ፦
ወይም ፡ ነፍስ ፡ ከሌለው ፡ ከወደቀ ፡ ሬሳ ፦
ከቶ ፡ ልዩነትህ ፡ በምን ፡ ላይ ፡ ነውሳ ?
“ በነሴ ፡ እነብሴ ፡ በነማይ ፡ በጎንቻ ፦
ወንዱ ፡ ሁል ፡ ሴት ፡ ሆኖ ፡ ከቀረ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፦
ለቀማኞች ፡ መቅጫ ፡ ላመጸኞች ፡ መግቻ ፦
ለደካሞች ፡ ምሽግ ፡ ጋሻ ፡ መመከቻ ፦
ለስ ፡ ተሽከሚ ፡ ውሀ ፡ በቅምጫና ፡ ጥሬ ፡ በስልቻ ፦
እንኮዋን ፡ በማውቀው ፡ ዱር ፡ በማውቀው ፡ ስርቻ ፦



ስሄድ ፡ አልኖርምወይ ፡ እስካገር ፡ ዳርቻ ፦
“ ሌሎች ፡ ሲበዪሉ ፡ እሱ ፡ መከፋቱ ፦
ሌላ ፡ ሰው ፡ ሲጠቃ ፡ እሱ ፡ መቆጣቱ ፦
የሰው ፡ ቁስል ፡ እሞት ፡ እንዲህ ፡ መሰቅየቱ ፦
ግፍንና ፡ አመጽን ፡ እንደ ፡ መርዝ ፡ መጥላቱ ፦
ሀይወቱን ፡ ለሰው ፡ መብት ፡ ዋጋ ፡ አርጎ ፡ መስጠቱ ፦
ግርማው ፡ እዳንበሳ ፡ ሲያዩት ፡ ማስፈራቱ ፦
ምን ፡ ከባህር ፡ አሸዋ ፡ ቢበዛ ፡ ጠላቱ ፦
ጎራዴውን ፡ መዞ ፡ አውጥቶ ፡ ካፎቱ
ብቻውን ፡ ብቅ ፡ ሲል ፡ መድረሻ ፡ ማጣቱ ፦
ሳያሰናክለው ፡ ጋሬው ፡ ቁልቁለቱ ፦
ሀይሉን ፡ ሳይቀንሰው ፡ ራቡ ፡ ጥማቱ ፦
ርቀት ፡ ሳይገታው ፡ እዳሳብ ፡ ፍጥነቱ ፦
እነሴ ፡ ነው ፡ ሲባል ፡ ጎንቻ ፡ መታየቱ ፦
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ባህሪ ፡ ይዞ ፡ መገኘቱ ፦
አይመስክርምወይ ፡ ሰው ፡ ከተሰራበት ፡ ከጎስቋላ፡ ጭቃ፡
ላለመሰራቱ ፦
ጥንቱኑ ፡ ሲፈጠር ፡ ሲወለድ ፡ ከናቱ ፦
የሰው ፡ ቤዛ ፡ እንዲሆን ፡ ታቦ ፡ ለመምጣቱ ፦
“ እየ ! ምን ፡ ያደርጋል ፡ ቢበንቱ ፡ መመኘት ፡ የማይ
ገኝ ፡ ነገር ፦
ባይሆንማ ፡ ኖሮ ፡ ሹመት ፡ እንደ ፡ ቂጥኝ ፡ የሚወረስ ፡
ከዘር ፦
ቅን ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ህዝብ ፡ ለማስተዳደር ፦
የያንዳንዱን ፡ ድሀ ፡ መብት ፡ ለማስከበር ፦
ለዚህ ፡ ለተጠቃ ፡ ለተበደለ ፡ አገር ፦
መድሀኒት ፡ እዲሆን ፡ እሱን ፡ መሾም ፡ ነበር ፡”

“ ለሽፍታ ፡ የሚሆን ፡ አይመስለኝም ፡ እንጂ ፡ ግጥሙ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ እኔ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንደምነግራችሁ ፡ ባላገር ፡ ሀይለኛ ፡ የሚወድ ፡ መሆኑን ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳይ፡ ነው ።” አሉ ፡ ፊታውራሪ ። “እየ ፡ ጉድ ! እዩዋቸው ፡ የኛን ፡ ከንቱ

ሮጬ ፡ ደስ ፡ ባለኝ ፡ ብዬ ፡ እመኘለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልችልም !
ጉዋደኞቼ ፡ በዩስርጉ ፡ በየመትባሉ ፡ እንደያቅማቸው ፡ እኒ
ጠው ፡ አንዳንዶቹ ፡ እመሀል ፡ ገብተው ፡ ባንገታቸው ፡ ሌሎች
አዳር ፡ ቆመው ፡ ግጥም ፡ እዩገጠሙ ፡ በቃላቸው ፡ እዩዘፈኑ ፡
የወጣትነት ፡ ስሜታቸውን ፡ ሲገልጹና ፡ የልብ ፡ እንፋሎታቸው ፡
ሲወጣላቸው ፡ ስመለከት ፡ እኔም ፡ እንደነሱ ፡ ተነስቼ ፡ ባንገቴ ፡
ወይም ፡ ግጥም ፡ እዩገጠምሁ ፡ ቢቃሌ ፡ ዘፍኜ ፡ እንዲወጣልኝ ፡
ደስስስ ፡ እንዲለኝ ፡ በጣም ፡ እመኛለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነማማና ፡
ከናባባ ፡ ከሮጌዎቹ ፡ ጋር ፡ ተቀምጦ ፡ መመልከት ፡ እንጂ ፡ እን
ዲህ ፡ ማድረግ ፡ አልችልም ! ሌላው ፡ ይቅርና ፡ እዚህ ፡ ቤት ፡ ከሚ
መጡት ፡ ዘመዶቻችን ፡ ጋር ፡ ካልሆነ ፡ ከሌላ ፡ ጋር ፡ አንገቴን ፡
ቀና ፡ አድርጌ ፡ እንድናገር ፡ ወይም ፡ እንድስቅና ፡ እንድጫወት ፡
እንኳዋ ፡ አይፈቀድልኝም ! ሀአ ፡ የጌታ ፡ ልጅ ! የጌታ ፡ ልጅ ፡ መ
ሆን ፡ እንዲህ ፡ እንዩኔ ፡ ታስሮ ፡ መኖር ፡ የሚወዱትን ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ መመኘት ፡ እንጂ ፡ ማድረግ ፡ አለመቻል ፡ ከሆነ ፡ ከቅጣት ፡
ሁሉ ፡ የከፋ ፡ ቅጣት ፡ ከባርነት ፡ ሁሉ ፡ የከፋ ፡ ባርነት ፡ ነው !»
አለች ፡ በሻከረ ፡ ድምጽ ፡ የኑሮዋን ፡ ሁኔታ ፡ ስትዘረዝር ፡ ስቃዩ ፡
ተሰማትና ፡ አይኖችዋ ፡ እንባ ፡ ቋጥረው ።

«የለም ፤ እንደሱ ፡ አይደለም ፡ አይዞሽ ፡ ሆድ ፡ አይባስሽ !»
አለ ፡ በዛብህ ፤ የተዋበ ፡ ፊትዋን ፡ ለልብዋ ፡ የተሰማው ፡ መሪር ፡
ሐዘን ፡ ማበላሸት ፡ መጀመሩን ፡ አይቶ ፡ የሚለው ፡ ቅጡ ፡ ጠፋ
ውና ።

«ከነጻነት ፡ ወደ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ የገባሁበት ፡ ቀን ፡ ምንም ፡
ሩቅ ፡ ቢሆን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ትዝ ፡ ሲለኝ ፡ ይኖራል !» አለች ፡ ቀጠ
ለችና ፡ ልቅሶዋን ፡ ለመዋጥ ፡ እዩታገለች ።

«ምናልባት ፡ የስድስት ፡ አመት ፡ ልጅ ፡ብሆን ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡
አልበልጥም ።» እጎረቤታችን ፡ እስካለ ፡ የምትባል ፡ ጉዋደኛየ ፡
ነበረች ። ምናልባት ፡ አንድ ፡ አመት ፡ ትበልጠኝ ፡ ይሆናል ። ዛሬ ፡
አራት ፡ ወይም .....አምስት ፡ ልጆች ፡ ወልዳ ፡ ትልቅ ፡ ሴት ፡ ሆና
ለች ።አንድ ፡ ቀን ፡ ስንጫወት ፡ ተጣላንና ፡ ታገልን ፡ እጭቃ ፡
ውስጥ ፡ ጥላ ፡ ፊቴን ፡ በጥፍርዋ ፡ በጭጭራ ፡ አደማችኝ ። ከዚያ ፡
እያለቀስሁ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ስመጣ ፡ ክፉ ፡ አጋጣሚ ፡ አባባ ፡ ከሰ



ዎች ፡ ጋር ፡ እበር ፡ ቆመው ፡ ሲነጋገሩ ፡ ነበርና ፡ በጭቃ ፡ ተነከሬ፡
ፉቴ ፡ ደምቶ ፡ ሲያዩ ፡ እብደ ፡ ሆኑ ። ወዲያው ፡ የልጅቱን ፡ አባት፡
አስጠርተው ፡ ሊደበድቡት ፡ሲሉ ፡ ሰዎች ፡ ገላግለው ፡ ሁለተኛ ፡የ
ሱም ፡ ልጅ ፡ ሆነች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ አጠገቤ ፡ እንዳይደርሱ ፡
አስጠንቅቀው ፡ ማሩት ። ከዚያ ፡ እያ ፡ ጣሹ ፡ የልጅቱ ፡ አባት ፡
እቤቱ ፡ ሄዶ ፡ ልጁን ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ገላዋ ፡ ሁሉ ፡ እስኪ
ቆስል ፡ ገረፋት ። እኔም ፡ ያነለት ፡ ክፉኛ ፡ ተመትቼ ፡ ከመንደሩና፡
ካሽከሮች ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ስጫወት ፡ የተገኘሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የ
ባሰ ፡ ቅጣት ፡ የሚደርስብኝ ፡ መሆኑን ፡ አባባ ፡ አስጠነቀቁኝ ።
ታውቃለህ ? ያነለት ፡ አባባ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ የተቆጡት ፡ ልጅቱ ፡
እኔን ፡ ስለመታችኝ ፡ አይደለም ፡ እሳቸው ፡ ስለተደፈሩ ፡ ነው !”
አለች ፡ ሰብለ ፡ አይኖችዋ ፡ ሳይረግቡ ፡ በዘገነ ፡ እንዳሉ ፡ ያዘን ፡
ፈገግታ ፡ ፈገግ ፡ ብላ ። «እንዴት ፡ ብደፈር ፡ ነው ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ በ
ጭቃና ፡ በደም ፡ የምትነከረው ?» ያሉት ፡ ሁልጊዜ ፡ ይታሰበኛል!
በበነጋው ፡ ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ እንደልማዳቸው ፡ ካጥራችን ፡ ውጭ ፡
እየተንጫጩ ፡ ሲጫወቱ ፡ ሰማሁና ፡ ትናንት ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡
ረስቼ ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ለመድረስ ፡ ቸኩዬ ፡ ልብሴን ፡ እንኩዋ ፡
በቅጡ ፡ ሳልለብስ ፡ እዩሮጥሁ ፡ በሄድ ፡ ገና ፡ ከሩቅ ፡ ሲያዩኝ ፡ የሚ
ባላ ፡ አውሬ ፡ እንደመጣባቸው ፡ ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሸሹ ።
ያነለቱ ፡ ድንጋጤየ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አብሮኝ ፡ ይኖራል ! ከሰው ፡ የተ
ለየሁ ፡ ሰው ፡ የሚሸሸኝ ፡ ፍጡር ፡ መሆኔን ፡ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡
መገንዘብ ፡ የጀመርሁበት ፡ ቀን ፡ ስለሆነ ፡ አልረሳውም ! አብ
ሮኝ ፡ ይኖራል !» አለች ፡ አሁንም ፡ ቅርታ ፡ ባስጌጠው ፡ ፊት ፡
አይኑዋን ፡ በዘዝ ፡ አድርጋ ፡ ከስራ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ልጆቹ፡
እርስዋን ፡ ፈርተው ፡ የሮጡት ፡ ሩጫ ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ እዩታያት ።
«ከዚያ ፡ ደንግጠሁ ፡ ስቆም ፡ እነሱ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ወደኔ፡
እየተመለከቱ ፡ በጆቻቸው ፡ ወደኔ ፡ እየመለከቱ ፡ ይነጋገሩ ፡ ጀመር ።
እንደገና ፡ ቆሙልኝ ፡ ብዬ ፡ ወደነሱ ፡ ስሮጥ ፡ እነሱም ፡ እንደ ፡
ገና ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሮጡና ፡ እንደፊቱ ፡ አለመቆሜን ፡ ሲያዩ ፡ ወደ
ዩቤታቸው ፡ ተበታተኑ ። እኔ ፡ እስካለን ትናንት ፡ የመታችኝን ፡
ልጅ ፡ ተከትዬ ፡ እስከ ፡ ቤትዋ ፡ እየሮጥሁ ፡ ሄድሁ ። አለቅስ ነበር።
ከዚያ ፡ ያስካለ ፡ እናት ፡ እቱቱ ፡ ደብረቱ ፡ ያዙችኝና ፡ እንባዩን ፡

ሁሉ ፡ የደረሰው ፡ ባንተ ፡ ጥፋት ፡ ነውና ፡ ለጉልቶቹ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሌላ ፡ በርታ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ቢደረግ ፡ ይሻላል !” እንደሚል ፡ አይጠረጠርም ። ታዲያ ፡ ሽክም ፡ ሆኖ ፡ የኖረን ፡ የሰለቸን ፡ ዘመድ ፡ በቀጥታ ፡ አፍ ፡ አውጥቶ ፡ ወግድልኝ ፡ ከማለት ፡ የጋራ ፡ ዘመድ ፡ ተሰብስቦ ፡ በጥፋቱ ፡ ፈርዶ ፡ ወግድለት ፡ ሲል ፡ አይሻልም ? አስር ፡ እጥፍ ፡ ይሻላል ! ዘመድን ፡ ወግድልኝ ፡ ከማለት ፡ ወግድለት ፡ የሚል ፡ ማግኘት ፡ ከሸክምም ፡ ከወቀሳና ፡ ከሜትም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ያድናል ።

ፊታውራሪ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ይህን ፡ ሲያሰላስሉ ፡ ቆዩና ፡ “ ደግ ፡ ነው ፡ አዳራሽ ፡ እስነጥፍና ፡ እንመካከርበት ! ” አሉ ፡ ወደ ፡ መሰረት ፡ ዘወር ፡ ብለው ።

ያነሰት ፡ ዘመቻው ፡ ቀርቶ ፡ አዳራሽ ፡ ተነጥፎ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጆች ፡ ከያሉበት ፡ እዬተፈለጉ ፡ ተጠርተው ፡ ተሰበሰቡ ። ጉዱ ፡ ካሳም ፡ ባላገር ፡ ስላደረገው ፡ አድማ ፡ ለመመካከር ፡ እፊታውራሪ ፡ ቤት ፡ የዘመድ ፡ ስብሰባ ፡ መደረጉን ፡ ስለሰማ ፡ መቾም ፡ ዘመድ ፡ ነውና ፡ ወግድ ፡ የማይባል ፡ መሆኑን ፡ በማወቁ ፡ ምንም ፡ ባይጠራ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ለመቀላወጥ ፡ ሄዶ ፡ ተጨመረ ።

“ በሉ ፡ ለኔ ፡ የነገራችሁኝን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሳታስቀሩ ፡ ለዘመዶቻችን ፡ ንገሩዋቸው ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ባላገር ፡ አስሮ ፡ ያሰነበታቸውን ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ እያግድገው ፡ በተራ ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ከቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ባይናቸው ፡ ገርፈው ። ካምስቱ ፡ አሽከሮች ፡ ማን ፡ እንደሚናገር ፡ እስበሳቸው ፡ ሲተያዩና ፡ አንተ ፡ ተናገር ፡ አንተ ፡ ተናገር ፡ ሲበባሉ ፡-“ በሉኮ ፡ ተናገሩ ! እድሜ ፡ ለቀኛዝማች ፡ አካሉ ! እድሜ ፡ ለክብሬና ፡ ለጥቅሜ ፡ ታጥቆ ፡ ለቆመው ፡ ወንድሜ ፡ ለቀኛዝማች ፡ አካሉ ! ባላገር ፡ ከጉልቴ ፡ የሚያገኘውን ፡ እንጀራ ፡ እዬበላ ፡ ጠግቦ ፡ ጉሽን ፡ እዬጠጣ ፡ ሰክሮ ፡ ባደባባይ ፡ የሰደበኝን ፡ ያዋረደኝን ፡ እኔን ፡ ሽሮ ፡ በጉልቴ ፡ ሀሀሀሀ -- በጉልቴ ፡ አበጆ ፡ በለውን ፡ መሾሙን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ጉድ ፡ ለዘመዶቻችን ፡ ንገሩዋቸውና ፡ ከወንድሜ ፡ ከቀኛዝማች ፡ አካሉ ፡ ጋር ፡ ይፍረዱን ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ የገዛ ፡



ንግግራቸውን ፡ በሰሙ ፡ መጠን ፡ ስሜታቸው ፡ ምርር ፡ ንግግራቸው ፡ ክርር ፡ እያለ ።

ከዚያ ፡ ካምስቱ ፡ አሽከሮች ፡ መሀከል ፡ ደስታ ፡ የሚባለው ፡ ለነገሩ ፡ መግቢያ ፡ እንዲሆነው ፡ እነሱ ፡ እንደሚት ፡ እንደ ፡ ተያዙ ፡ ለመናገር ፡ ሲጀምር ፡- “ ያንተን ፡ መያዝ ፡ አልጠዬቅሁህም ! አንተ --- እናንተ ፡ ብትያዙ ፡ ባትያዙ ፡ ጉዳዬ ፡ አይደለም ! እኔ ፡ የጠዬቅሁህ ፡ ሌላ ፡ ነው ! ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አቋርጠው ። ወዲያው ፡ ደስታ ፡ የኒታውን ፡ ቁጣ ፡ ስላዬ ፡ ደንግጦ ፡ ድንግርግር ፡ ሲለው ፡ ፈረደ ፡ የሚባለው ፡ ሎሌ ፡ ጉዋደኛው ፡ ተመለከተና ፡ ከፉ ፡ ነጠቅ ፡ አድርጎ ፡- “ መቼም --- መቼም ፡ በሶስቱ ፡ ጉልቶቻችን ፡ ከሚኖረው ፡ ህዝብ ፡ ከህጻናትና ፡ ከበሽተኞች ፡ በቀር ፡ ወንድ ፡ የተባለ ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ተሰብስቦ ፡ በጌቶች ፡ ላይ ፡ ያወርደው ፡ የነበረውን ፡ ስድብና ፡ ርግማን ፡ እንከዋን --- ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ ለመናገር ፡ መጀመሪያም ፡ ለምን ፡ ሰማሁ ፡ ያሰኛል ። ስለዚህ --- ባልናገር ፡ ይሻላል ! ብቻ ፡ ከስድቡም ፡ ከርግማኑም ፡ በሁዋላ ፡ የሚባሉ ፡ ሰዎች ፡ ቢኖሩ ፡ ነገራቸውን ፡ እዚያው ፡ የዘመድ ፡ ዳኞች ፡ እዬመረጡ ፡ እንዲጨርሱ ፡ እንጂ ፡ ተካሰው ፡ ወደ ፡ ጌቶች ፡ እዬመጡ ፡ ዳኝነትና ፡ ውርርድ ፡ እንዳይከፍሉ ፡ በምንም ፡ ምክንያት ፡ መተያየና ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ወይም ፡ ያመትባል ፡ መዋያ ፡ ይዞ ፡ ወይም ፡ ቤትና ፡ አጥር ፡ እሰራለሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ጌቶች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳይመጣ ፡ ከውስጥም ፡ ሆነ ፡ ከውጭ ፡ ሌባና ፡ ቀማኛ ፡ ቢነሳ ፡ ለሶስቱም ፡ ጉልቶች ፡ የጎበዝ ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ የተሾመው ፡ አበጆ ፡ በለው ፡ የተነሳውን ፡ ሌባና ፡ ቀማኛ ፡ አድኖ ፡ **እንዲይዝ** ፡ ከበጆ ፡ በለው ፡ ያመለጠ ፡ ሌባና ፡ ቀማኛ ፡ ቢኖር ፡ አገር ፡ ተሰብስቦ ፡ በውስ ፡ አውጥቶ ፡ ለጎበዝ ፡ አለቃው ፡ እንዲያስረክብ ፡ ከዚህ ፡ የወጣ ፡ የሚሰራ ፡ ሰው ፡ ቢኖር እንደ ፡ ከሀዲ ፡ እንዳገር ፡ ጠላት ፡ ተቆጥሮ ፡ ቢታመም ፡ ጠያቂ ፡ ቢሞት ፡ ቀባሪ ፡ እንዳያገኝ ፡ ከተወሰነ ፡ በሁዋላ ፡- ከበተከሲያን ፡ መጣፍ ፡ ሠጥቶ ፡ ሁሉም ፡ መጣፉን ፡ እዬጠፋ ፡ ማለና ፡ በመጨረሻ ፡ ቁስ ፡ ተነስተው ፡ “ከዚህ ፡ ከማላችሁበት ፡ ብትወጡ ፡ ውግዝ ፡ ከማሪያስ” ብለው ፡ ገዘቱ ። ብቻ ፡ ቁሱ ፡ ተገደው ፡ ነው ፡ አሉ!” ፡

አሙስ ፡ ጥዋት ፡ ልኩራ ፡ በሁሉ ፡ እንደ ፡ ታዘዘችው ፡ ገና ፡ ሰማይ ፡ መሬት ፡ ሳይለቅ ፡ ውሀዋን ፡ አሙቃ ፡ እመቤትዋን ፡ ቀሰቀሰቻቸው ። ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ሌሊቱን ፡ እንቅልፍ ፡ እንቢ ፡ ብሎዋቸው ፡ ሲወራጩ ፡ አድረው ፡ እንጋት ፡ ላይ ፡ ተኝተው ፡ ነበረና ፡ ልኩራ ፡ ስትቀሰቅሳቸው ፡ በጣም ፡ ደንግጠው ፡ ስለተነሱ ፦

"ስግልፋዲስ ፡ ቂዲስዲስ ! አይዞ ፡ ቲደንጊጥ ፡ ኢሜቴ ፡ ሁንንጋና ፡ ወፍጫጫትና ፡ ሁንንጋና ፡ ሜራቲንሳማ ፡ ላቃቃትና! አለች ፡ ልኩራ ፡ እመቤትዋ ፡ ደንግጠው ፡ ሲነሱ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ እንዳያጣረራቸው ፡ ስመ ፡ እግዚአብሄር ፡ ጠርታ ።

ወዲያው ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ቶሎ ፡ ተነስተው ፡ ውጭ ፡ ደርሰው ፡ ተመለሱና ፡ ራሳቸውን ፡ በሙቅ ፡ ውሀና ፡ በሳሙና ፡ ሙልጭ ፡ አድርገው ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ታጥበው ፡ ጠጉራቸው ፡ ደርቆ ፡ እንዳይንጨበረር ፡ በፊት ፡ ማታቸው ፡ ከንጥሩ ፡ ቅቤ ፡ ትንሽ ፡ ቆንጠር ፡ አድርገው ፡ በመሀል ፡ እጃቸው ፡ ሰብቀው ፡ አሸሸሸት ፡ አደረጉና ፡ ተበጥረው ፡ ፊታቸውን ፡ በመስተዋት ፡ ሲመለከቱ ፡ ጊዜ ፡ የድሮዋን ፡ ካስራምስት ፡ አመት ፡ በፊት ፡ የሚያዋቁዋትን ፡ የሰራሽን ፡ አዩ ፡ ያስራምስት ፡ አመት ፡ እድሚያቸው ፡ ከቅቤው ፡ ጋር ፡ በሙቅ ፡ ውሀና ፡ በሳሙና ፡ ታጥቦ ፡ እንደሄደ ፡ ሁሉ ፡ የሰላሳ ፡ አምስት ፡ አመት ፡ የሰራሽ ፡ እመስተዋቱ ፡ ውስጥ ፡ አዩና ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ከዚያ ፡ ተነስተው ፡ ጥልፍ ፡ ቀሚሳቸውን ፡ ለበሱና ፡ የተወለወለውን ፡ ጌጣጌጥ ፡ አቅርበው ፡ ወርቅ ፡ መስቀላቸውን ፡ እልቅታቸው ፡ ላይ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ እየተሰባጠረ ፡ የተሰካ ፡ አሸንክታባቸውን ፡ እያረታቸው ፡ ላይ ፡ ከዚያ ፡ ትንሽ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ አሁንም ፡ እያረታቸው ፡ ላይ ፡ የወርቅ ፡ ሸብ ፡ ድሪያቸውን ፡ ከዚያ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ከዘና ፡ አቅፎ ፡ በዩበታው ፡ እንዲይዝ ፡ ከባድ ፡ ብር ፡ መስቀል ፡ የተንጠለጠለበት ፡ ድሜራ ፡ ማተባቸውን ፡ በንገታቸው ፡ አድርገው ፡ ወርቅ ፡ ጉትቻዎቻቸውን ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ጆሮዎቻቸው ፡ ብር ፡ አምባራቸውን ፡ በክንዳቸው ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ቀለበቶቻቸውን ፡ በጣቶቻቸው ፡ አልበና ፡ ድሪ ጃቸውን ፡ በግራቸው ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ መስቀል ፡ ደሙራ ፡



በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጥ ፡ አጊጠው ፡ አምረው ፡ ስታያቸው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አላትና ፦

"ኡኡ - - - ኢሜቴ ፡ ኢሜቴ ፡ ኢንዴት ፡ ኢንዴት ፡ ናምራለች!ኢንዴት ፡ ኢንዴትን ፡ ጉማለች!" አለች ፡ ልኩራ ።

"አምራለሁ ? ልኩራ !" አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽም ፡ አገልጋያቸው ፡ ስታሞግሳቸው ፡ በበኩላቸው ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ። መቼም ፡ ምስጋና ፡ ከየትም ፡ ቢመጣ ፡ የተመሰገኙን ፡ ልብ ፡ በደስታ ፡ መማረኩ ፡ አይቀርም ።

ከዚያ ፡ ልኩራ ፡ በሁሉ ፡ ያደረ ፡ እንጀራ ፡ በትኩስ ፡ የቅቤ ፡ ሽሮ ፡ አቅርባላቸው ፡ ትንሽ ፡ በሉና ፡ አንድ ፡ ብርሌ ፡ ማለፊያ ፡ ጠላ ፡ ጠጥተው ፡ ቡና ፡ ስትቀዳላቸው ፡ "ቲኒሽን ፡ ቂቤ ፡ ጨምራለሽ ፡ ጠጣች ፡ ኢሜቴ ፡ ሁዋጢምትን ፡ ከልክልልሻል!" አለች ።

"ታዲያ ፡ ቅድም ፡ አብረሽ ፡ አታቀርቢም ፡ ኖረሻል?አሀዮ! በይ ፡ አሁንም ፡ ቶሎ ፡ አምጭልኝ ፡ ሰዎች ፡ መምጫቸው ፡ ደርሶዋል!"

ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ቁርሳቸውን ፡ አድርገው ፡ ታጥቀው ፡ እቃቸውን ፡ ሁሉ ፡ አሰናድተው ፡ ሲጠብቁ ፡ አርፍደው ፡ በመጨረሻ ፡ አንድ ፡ አሽከር ፡ የሚቀመጡባትን ፡ በቅሎ ፡ እዩሳበ ፡ አራት ፡ የፈታውራሪ ፡ ቤት ፡ አሽከሮች ፡ ለዩስራቸው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እቃ ፡ የሚታዘለውን ፡ አዝለው ፡ የሚንጠለጠለውን ፡ አንጠልጥለው ፡ ደረሱ ።

"ጉዋዙ ፡ ቀድሞዋልና ፡ ሳይርቅ ፡ እንድረስበት ፡ እመይቴ !"አለ ፡ በቅሎ ፡ እዩሳበ ፡ የመጣው ፡ አሽከር ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽን ፡ እጅ ፡ ከነሳ ፡ በሁዋላ ። ወዲያው ፡ ተሸክሞ ፡ እበቅሎዋ ፡ ላይ ፡ ሲያስቀምጣቸው ፡ ወይዘሮ ፡ የሰራሽ ፡ ውሎ ፡ ገባ ፡ እንደሚሄዱ ፡ ሁሉ ፦

" ልኩራ ፡ ቤቱን ፡ ደህና ፡ አድርገሽ ፡ ስትጠብቂ ፡ እንድትቆይኝ ፡ ዋእ---እንች ፡ ቅንዳሻም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ተበላሽቶ ፡ አገኝና ፡ ልብ ፡ አርጊ !" ብለው ፡ በጉዋዙ ፡ ለመድረስ ፡ በቅሎዋቸውን ፡ አስገሩ ።

" ሂጂዲያ ! ቂንዳሽ ፡ ቂንዳሽ ፡ ላለች ፡ ኢስዋን ፡ ቂንዳሽ!" አለች ፡ ልኩራ ፡ እመቤትዋ ፡ በቅሎዋን ፡ እያስገሩ ፡ ሲሄዱ፡

ወራሪዋን ፡ ዘራፊዋን ፡ ተቀበለች ። ባገሩ ፡ ወንድ ፡ እንዳልተፈጠረ ፡ ሴቱ ፡ ከሴት ፡ እየተጋባ ፡ እንደሚወልድ ፡ ሁሉ ፡ በዩዶጁ ፡ እንደ ፡ መቃብር ፡ ሀውልት ፡ ሳይንቀሳቀስ ፡ ሳይተነፍስ ፡ ዝም ብሎ ፡ ሰፍሮ ፡ ወራሪውን ፡ ዘራፊውን ፡ የሚመለከት ፡ ሴትና ፡ ልጅ ብቻ ፡ ነበር ። ጉሊትም ፡ እንደናሞራ ፡ ከወራሪው ፡ ተርፎ ፡ አውሬውን ፡ ውሻውንና ፡ አሞራውን ፡ የሚመግብ ፡ ፍሪዳና ፡ በግ ፡ ታርዶ ፡ ብዙ ፡ ድቄስና ፡ ቅቤ ፡ ጠላና ፡ ጠጅ ፡ ማር ፡ ተዘርፎ ፡ ለወራሪና ፡ ላውሬ ፡ ትልቅ ፡ ድግስ ፡ ሆና ፡ ሰነበተ ። የጉሊት ፡ ሴቶችና ፡ ልጆችም ፡ እንደናሞራ ፡ ሴቶችና ፡ ልጆች ፡ እየታሰሩ ፡ እየተገረፉ ፡ ወንዶቻቸው ፡ ያሉበትን ፡ እንዲናገሩ ፡ ተጠየቁ ፡ ብቻ ፡ ከባላገር ፡ አፍ ፡ ትንሽ ፡ ምስጢር ፡ ከማውጣት ፡ ከጀርባው ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ማውጣት ፡ ስለሚቀል ፡ ፊታውራሪ ፡ የባላገርን ፡ ሴቶችና ፡ ልጆች ፡ እያስገረፉ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ አወጡ ፤ ምስጢር ፡ ግን ፡ ትንሽም ፡ አላገኙ !

ፊታውራሪና ፡ ወራሪ ፡ ሰራዊታቸው ፡ ጉሊት ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ቆይተው ፡ ከባላገር ፡ ሀብት ፡ ሊያዝ ፡ የሚቻለውን ፡ ይዘው ፡ ሊያዝ ፡ የማይችለውን ፡ አበላሽተው ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ጎርጎር ፡ ለማለፍ ሲሰናዱ ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ ባላገር ፡ ራሱን ፡ ተከናንቦ ፡ ከጎርጎር ፡ በኩል ፡ መጥቶ ፡ እንደሚሰልል ፡ ቁጥቁዋጦ ፡ ተተግኖ ፡ የፊታውራሪን ፡ ሰፈር ፡ ሲመለከት ፡ ቆዩና ፡ እንደገና ፡ ወደመጣበት ፡ ተመልሶ ፡ እየተገላመጠ ፡ እያየ ፡ ሲሄድ ፡ — ኢጋፋሪ ፡ መሰረትና ፡ ሌሎች ፡ አሽከሮች ፡ አስቀድመው ፡ አይተውት ፡ ተጠንቅቀውበት ፡ ስለነበረ ፤ ፈረሰኛ ፡ ልከው ፡ አስይዘው ፡ አስመጡት ።

እስረኛው ፡ የፊቱን ፡ ታስሮ ፡ እፊታውራሪ ፡ ፊት ፡ ሲቀርብ ፡ እንደ ፡ ጎመገ ፡ አውሬ ፡ ደሙን ፡ ለማየት ፡ ቸኩለው ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየተንቆራጠጡ ፡ አንድ ፡ ጥያቄ ፡ እንኳዋ ፡ ሳይጠይቁ ፡ "ጣልልኝ ! ጣሉና ፡ በለው !" አሉ ።

"ጌታዩ ፡ በሽተኛ ፡ ነኝ ፡ ተገርፌ ፡ አልተርፍም ፡ እሞታለሁ ! የብዙ ፡ ልጆች ፡ አባት ፡ በጅዎ ፡ ብሞት ፡ አሳዳጊ ፡ የሌላቸው ፡ ልጆቼ ፡ በእግዚአብሄር ፡ ዘንድ ፡ ያስጠይቁዎታል ! እባክዎ ፡ አያስገርፉኝ ፡ ተገርፌ ፡ የምናገረውን ፡ ሳልገረፍ ፡ ልናገር !" አለ ፡ እስረኛው ።

"የምትናገረው ፡ እውነት ፡ ለመሆኑ ፡ ምን ፡ መተማመኛ ፡



አለ ?"

"የሚጠይቁኝን ፡ ከተናገርሁ ፡ በሁዋላ ፡ እስረኛ ፡ አድርገው ፡ ይያዙኝና ፡ እውነት ፡ ሳይሆን ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ያን ጊዜ ፡ ይግረፉኝ ።"

"ባል ፡ ንገረን ፡ የማን ፡ ሰላይ ፡ ነህ ?"

"ሰላይ ፡ አይደለሁም ፡ የዚህ ፡ አገር ፡ ባላገር ፡ ነኝ ። ጌታዩ ፡ የሶስቱን ፡ ጉልትዎን ፡ ባላገር ፡ ሊመቱ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተወራ ፡ ምን ፡ እናድርግ ፡ ብሎ ፡ ለመመካከር ፡ ሮብ ፡ የሶስቱም ፡ ጉልቶች ፡ ባላገር ፡ እናሞራ ፡ ተሰብስቦ ፡ መስማማት ፡ ስላቃተው ፡ አሁንስ ፡ እዚህ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ወስኖ ፡ ተለያዩ ። እዚህም ፡ በተደረገው ፡ ስብሰባ ፡ ስምምነት ፡ ሳይገኝ ፡ ቀርቶ ፡ በበነጋው ፡ ጎርጎር ፡ ላይ ፡ እንደገና ፡ እንሰብሰብ ፡ ስለተባለ ፡ እዚያ ፡ ተሰብስበን ፡ ሰንብተን ፡ ከዚያ ፡ መምጣቴ ፡ ነው ።"

"እኮ ፡ ልትሰልል ፡ አይደለም ፡ የመጣህ ?"

"አይደለም ።"

"ታዲያስ ?"

"እሶስቱም ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ስብሰባ ፡ ስምምነት ፡ አልተገኘም ። የናሞራ ፡ ህዝብ ፡ ባበጀ ፡ በለው ፡ መሪነት ፡ እንዋጋ ፡ ባይ ፡ ሆነ ። የዚህ ፡ የጉሊት ፡ ህዝብ ፡ የታቦት ፡ አማላጅና ፡ መተያያ ፡ ይዘን ፡ ከጌታችን ፡ እንታረቅ ፡ አለ ። የጎርጎር ፡ ህዝብ ፡ በሁለት ፡ ተከፍሎ ፡ ግማሹ ፡ እንዋጋ ፡ ሲል ፡ ግማሹ ፡ እንደ ፡ ጉሊት ፡ ህዝብ ፡ መታረቅ ፡ ፈለገ ። በሶስቱም ፡ ስብሰባ ፡ ህዝቡ ፡ እንዲሁ ፡ በሁለት ፡ ተከፍሎ ፡ ሲንጨቃጨቅ ፡ ሰንብቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ጌታችን ፡ እናሞራን ፡ መትተው ፡ እዚህ ፡ መድረስዎ ፡ ስለተሰማ ፡ ጉሊቶች ፡ በሙሉ ፡ አገራችንን ፡ አናስበድልም ፡ ሄደን ፡ ጌታችንን ፡ ይማሩን ፡ እንላለን ፡ ብለው ፡ ከስብሰባው ፡ ወጡ ። አሁን ፡ ሁሉም ፡ ይመጣሉ ። እኔ ፡ ቀድሜያቸው ፡ መጥቼ ፡ እዚህ ፡ ከደረስሁ ፡ በሁዋላ ፡ የጌታዩን ፡ ሰፈር ፡ ሳይ ፡ ስለፈራሁ ፡ እነሱ ፡ እስኪደርሱ ፡ ዘወር ፡ ብዬ ፡ ለመቆየት ፡ ወደ ሁዋላ ፡ ስመለስ ፡ ነው ፡ የተያዝሁ ።"

"አሁን ፡ እናበጀ ፡ በለው ፡ ጎርጎር ፡ ናቸው ?"

"የሉም ፡ አበጀ ፡ በረው ፡ እናሞሮችን ፡ ከጎርጎርም ፡

